# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)


ግንቦት 25 ቀን 2002 ዓ.ም

## ለሀቀኛ ሀገር ወዳድ ድርጅቶች ሁሉ ጥሪ

## በጋራ ቆራጥ ትግል ወያኔን እናስወግድ!

ሀገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ አስከፊ በሆነ ደረጃ፤ አሳሳቢ በሆነ ማጠፊያ ላይ ደርሳለችና ለሀቀኛ ሀገር ወዳዶች ሁሉ የጀግንነት፣ የጎበዝ ያለህ/ያለሽ ብሎ ጥሪ ማሰማቱ ግዴታ ሆኗል። የወያኔ ቡድን በዚህም በዚያም ጦርነቶችንም ቀስቅሶ፤ የአንድ ድርጅት ዘረኛ አገዛዝን በግልጽ አስፍኖ ሊቀጥልብን ተነስቷልና ይህን በጊዜ ማስቆሙ የሀገር ማዳኑ ትግል ዋና ተልዕኮ ሆኖ ይገኛል። የወያኔን አገዛዝ መጣሉና ማስወገዱ ደግሞ ትላንት መገባደድ ያለበት ሥራ ነበርና ዛሬም አቢይ አድርገን ማንሳት መገደዳችን ድክመታችንን ጠቋሚ መሆኑን መካድ አንችልም። ከዚህ ባሻገር ግን ምንም ደም ሳይከፍሉ የማይጓዙበት ጎዳና መሆኑን ያወቅነውን ዛሬም ያዋጣል ብሎ መያዙ መጃጃል መሆኑን ሳይተኙ ሊቃዡ ለጨከኑትም ወያኔ ራሱ መልዕክቱን በግልጽ ሰሞኑን ሰጥቷል። ወያኔን በራሱ ፍርደ ገምድል ፍርድ ቤት ሊከሱ መነሳትም ሌላ ቅዠት ነው።

ባለፉት 19 ዓመታት ወያኔ በሥልጣን ሊቆይ የቻለው ተቃዋሚ ኃይሎችና ሕዝብን በማፈን ብቻ ሳይሆን በመከፋፈልም ነው። የተወሰኑ ተቃዋሚ ኃይሎችና መሪዎቻቸውም አውቀው ይሁን ተደናግረው ለዚሁ ለወያኔ ተንኮል ሰለባና ተባባሪም ሆነዋል። የህብረት ጥረቶችን በማደናቀፍ፤ ድርጅቶችን በመከፋፈልና የአንጃነት መርዝን በመርጨት፤ ለወያኔ ቧልቶች አጃቢ በመሆን፤...ወዘተ ሀገርንም ሕዝብንም የማይጠቅሙ ሥራዎች ተሰርተዋል።

ይህ ማከተም እንዳለበት ደግሞ በተለይ ዛሬ ወያኔ አጃቢ አልሻም ብሎ የአንድ ድርጅት አምባገነንነትን ባሰፈነበት ጊዜ በጣም ግልጽ ሆኗል። ይህንንም በመገንዘብ ኢሕአፓ ለሀቀኛ ሀገር ወዳድና ጸረ ወያኔ ድርጅቶች ሁሉ የትግል ጥሪውን ያቀርባል። ኢሕአፓ ካሁን በፊት ተደርገው ከነበሩት የኅብረት ጥረቶች ከገበየው ተመክሮ በመነሳት በአላማው ላይና በአወቃቀሩ ላይ የግንዛቤ መጣጣም በማይኖርበት፤ በደፈናው በስመ ተቃዋሚነት ምርቱን ከግርዱ ፍሬውን ከገለባው በቅጡ ሊለይ በማይችልበት ዴሞክራትና ሀገር ወዳድ እያሉ ትብብርን በመመኘት ብቻ ህብረት ግንባር በሚል መዋቅራዊ ትስስር ውስጥ መግባቱ በአሁኑ ጊዜ ወቅታዊና ጠቃሚ አይደለም ብሎ ቢያምንም፣ ጸረ ወያኔ ድርጅቶች ማለትም የወያኔ አገዛዝን በሁለገብ ትግል መወገድ አለበት ብለው የሚያምኑ ድርጅቶች ተቀራርበውና ተባብረው ሊታገሉ ይችላሉ፤ ይገባልም ብሎ ያምናል።

ይህን ትብብር ሊያደርጉ የሚችሉ ድርጅቶችም፡

- የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት ነው ብለው የሚያምኑ፤
- የወያኔ አገዛዝ በሁለገብ ትግል መወገድ አለበት ብለው የሚያምኑ፤
- ድርጅታዊ ህልውና ያላቸው ማለትም በተጨባጭ ትግሉ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ወይም ሊያደርጉ የሚችሉ

መሆን አለባቸው ብሎ ያምናል።

የኢትዮጵያ ሕዝብም--በሀገርም በባዕድም ያለው--መደገፍ የሚገባው ይህን መሰል ድርጅቶችን ነው ሲል ኢሕአፓ ያምናል።

በዚህም መሰረት

- በድርጅቶች መሀል እሳት የሚለኩሱትን ሰርጎ ገቦችና ከፋፋዮችንም ለመቋቋምና ክፍፍልን ለማስወገድ፤
- ጥረቶችን ለማስተባበር፤
- በሁለገቡ ትግል ሆነ በዲፕሎማሲያዊና ቅስቀሳው መስክ የተደጋገፈ ሥራን ለማከናወን፤
- በተባበረ ትግል የወያኔን አገዛዝ ዕድሜ ለማሳጠር

እንድንችል፣ በዚህ ጥሪ ዙሪያ እንገናኝና በጋራ እንምከር ሲል ኢሕአፓ ያሳስባል። ዝግጁነቱንም ይገልጻል።



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France